# ሕዝባችን የአክራሪዎች ሰለባ አይሆንም!

ዮሐንስ ኃይሉ

07/29/14

ኢትዮጵያ ውስጥ በኃይማኖት ስም የሚንቀሳቀሱ ቡድኖች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል። የኃይማኖት ለምድን ለብሰው ሕቡዕ የፖለቲካ አጀንዳን ለማሳካት ላይ ታች ማለትም እየተለመደ መጥቷል።

እነዚህ ቡድኖች አመቺ ሁኔታ ሲያጋጥማቸውም በተለያዩ የአፍሪካ አገራት የሽብር ተግባራትን በመፈፀም ፍላጎታቸውንና እምነታቸውን በኃይል ሌሎች ላይ ለመጫን ይንቀሳቀሳሉ። በአፍሪካ የኃይማኖት አክራሪነት ሥር ሰዶ በየኃይማኖት አማኞቹ ተቀባይነት ያገኘበት ሁኔታ ባይኖርም ብቅ ጥልም እያለ በማድረስ ላይ ያለው ጉዳት ሙሉ በሙሉ የተገታ አይደለም።

በናይጄሪያ፣ በግብጽ፣ በሶማሊያ፣ በኬንያ፣ በግብጽ፣ በኢትዮጵያ፣ በሊቢያና በሌሎች የአፍሪካ አገራት የኃይማኖት ሽፋን የተላበሰ እንቅስቃሴ ታይቷል። በአንዳንዶቹ የተጠናከረ የአክራሪዎች እንቅስቃሴ የታየ ሲሆን በሌሎቹ ደግሞ አልፎ አልፎ ብቅ ጥልም በማለት የሚገለጽ ነው።

በመሆኑም በአሁኑ ወቅት አሜሪካ ለዓለም አቀፉ የፀረ ሽብር ትግል በቁልፍ አጋርነት ጠቀሜታውን ግምት ውስጥ በማስገባት ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ወዳጅነት አጠናክራ እየቀጠለች መሆኑን ሲነገር እናዳምጣለን።

በሌላ በኩል ቻይናን ጨምሮ በምሥራቁ ክፍለ ዓለም የሚገኙ አገራት ደግሞ ከኢትዮጵያ ጋር ብቻ ሳይሆን ከአፍሪካ አገራት ጋር ያላቸውን ዘርፈ ብዙ ትብብርና ወዳጅነት አጠናክረው ለመቀጠል እንዲያስችላቸው የኢትዮጵያን ዲፕሎማሲያዊ ጠቀሜታ በውል በመገንዘባቸው ግኑኝነታቸውን በየጊዜው ጠበቅ እያደረጉት እንደሆነ በተለይም ከአዲሱ የአፍሪካ ህብረት ሕንፃ ምረቃ ጋር ተያይዘው የወጡ ዘገባዎች ያመለክታሉ።

በዚህም ማቢያ ኢትዮጵያ ፈፅሞ በተቃረነ የፖለቲካል አይዶሎጂ በሚመሩትና በጂኦግራፊካዊ አቀማመጣቸውም ሙሉ በሙሉ ተቃራኒ በሆነ አቅጣጫ በሚገኙት ክፍለ ዓለማት መንግሥታትና ሕዝቦች ዘንድ ያላት ተቀባይነትና ተፈላጊነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጎላ መጥቷል።

የበርካታ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች አገር የሆነችው ኢትዮጵያ በውስጧ ሠላምንና መረጋጋትን አስፍናና የሕዝቦቿን አንድነት አስጠብቃ እንዲሁም ልማትን የማፋጠን አጀንዳን በዋነኛነት ይዛ መንቀሳቀስ ከጀመረች እነሆ ድፍን ሃያ ዓመታትን አስቆጥራለች፡፡

በአገራችን በአሁኑ ወቅት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጎለበተ የመጣው መረጋጋት ፈጣን ልማትን በማረጋገጥ ከድህነት ለመውጣት ከሚደረገው የሕዝቦቿ ትግልና የመንግሥት ጥረት ጋር ተዳምሮ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ብቻ ሳይሆን በመላው አፍሪካ ጭምር የሠላም፣ የመረጋጋትና የእድገት ተምሣሌት ለመሆን ችላለች።

አገሪቱ በሁሉም ዘርፍ እያስመዘገበች ያለችው መጠነ ሰፊ ለውጥና እድገትም በሌሎች የአፍሪካ አገራት እንደ አርአያ እንድትወሰድ እያደረጋት ነው።

ለሕዝቦች ሕልውናና ደህንነት በቅድሚያ በአንድ አገር ውስጥ ሠላምና መረጋጋትን ማስፈን ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው በውል የተገነዘበችው ኢትዮጵያ ከሯሷ አልፋ በግጭትና ጦርነት ውስጥ ባሉ የአፍሪካ አገራትም ተመሳሳይ ሠላም ይሰፍን ዘንድ ባለፉት ዓመታት የሠላም አስከባሪ ኃይሏን በመላክ የበኩሏን ጥረት ስታደርግ ቆይታለች፡፡ አሁንም በማድረግ ላይ ትገኛለች፡፡

እንደ አብነት ላይቤሪያና ሩዋንዳን የመሰሉ የአፍሪካ አገራት ቀደም ሲል የተከሰቱባቸውን የእርስ በእርስ ጦርነቶችና ግጭቶች በሕዝቦቻቸውና በአገራቸው ላይ ያደረሱትን አለመረጋጋቶች መፍትሄ ለመስጠት ባደረጉት ጥረት ቅድሚያ የደረሰው የኢትዮጵያ ሠላም አስከባሪ ኃይል መሆኑን በዋቢነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

የኢትዮጵያ ሠላም አስከባሪ ኃይል በላይቤሪያና ሩዋንዳን የመሰሉ የአፍሪካ አገራት ለሠላም ማስከበር እገዛ በተሰማራበት ወቅት ከሠላም ማስከበር ተግባሩ በተጨማሪ

ችግኞችን መትከልን ጨምሮ በተለያዩ ሰብዓዊ ዘርፎች በመሰማራት ለእነዚህ አገራት ሕዝቦች ያለውን ወንድማዊ አጋርነት ማስመስከር ችሏል፡፡

ለሠራዊቱ ይህን መሰል መልካም ተግባርም በእነዚህ አገራት የነበሩ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ተወካዮች የእውቅና ሽልማት በሰጡበት ወቅት በንግግራቸው አስምረውበታል፡፡ ለእነዚህ የአፍሪካ አገራት ኢትዮጵያ የሰጠችው እገዛም አህጉራዊ አለኝታነቷንና አጋርነቷን ከማረጋገጥ በተጨማሪም አፍሪካዊ ክብርና ሞገስም አላብሷታል፡፡

ይህም የአገራችን መንግሥት ሠላምን የማስፈን በጎ ጥረቱና ሠላም ወዳድነቱ በአገሩ ብቻ ሳይወሰን አህጉራዊ ኃላፊነት የተሞላበት መሆኑን አረጋግጧል። ይህ መልካምና በጎ ተግባርም ኢትዮጵያን በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ዘንድ እውቅናንና አድናቆትን እንድታተርፍ አስችሏታል። ቀደም ባሉት ዓመታት በተጠቀሱት አገራት ባበረከተችው የሠላም ማስከበር አስተዋፅኦም በቅርቡ በሱዳን አቢዬ ግዛት ውስጥ ያለውን ሁኔታ ለማረጋጋት አሜሪካና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ኢትዮጵያን ከየትኛውም አገራት ይበልጥ ተመራጭ አድርገዋታል፡፡

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መድረክ ላይ አፍሪካውያን ተቀባይነታቸውና ተደማጭነታቸው ይበልጥ እየጎለበተ እንዲመጣ በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በኩል ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረገች ትገኛለች።

ታላቁ መሪ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በአፍሪካና በምዕራባውያን መካከል የነበረው የእርዳታ ሰጭነትና የተመፅዋችነት ግንኙነት ተቀይሮ አፍሪካ በዓለም አቀፍ ገበያ ፍትሃዊ የሆነ የንግድ ሚዛን እንዲፈጠርላትና ግንኙነቱም በመከባበርና በመተማመን ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ መቆየታቸው ይታወቃል።

በአገራችን ላይ ሻዕቢያ ማቆሚያ የሌለው የሽብርና ትንኮሳ ስትራቴጂ እየተከተለ መሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነው። ይህንን እኩይ ተግባሩን ለማሳካት ኢትዮጵያ ውስጥ ኦነግ፣ ኦብነግ፣ ግንቦት ሰባት፣ አርበኞች ግንባርና የመሳሰሉትን ጨምሮ ያልተጠቀመበት ፀረ ሠላም ተላላኪ ኃይል አለ ለማለት ያስቸግራል።

እነዚህ ኃይሎች በሻዕቢያ የሽብር ሥልጠና ተሰጥቷቸው፣ ምክርና የሎጂስቲክስ ድጋፍ ተደርጎላቸው፣ በአገሪቱ የሚካሄድን ዓለም አቀፍ ጉባኤ እንዲያጨናግፉ አሊያም ሠላሟን እንዲያደፍርሱ ታዝው ከገቡ በኋላ በሕዝብና በመንግሥት ጥረት ተልዕኳቸው ተጨናግፎ እነሱም በቁጥጥር ሥር ሲውሉና በሚሰጡት ቃለ ምልልስ ይህንን እኩይ ተግባራቸውን ሲያረጋግጡ ለበርካታ ጊዜያት በሚዲያዎች ተመልክተናል።

እነዚህ የተለያዩ የሽብር ሙከራዎች ለበርካታ በተደጋጋሚ ጊዜያት እየተሞከሩ ይክሸፉ እንጂ ሁኔታውንና መልኩን እየቀያየረ ይህን ጠብ አጫሪና ነውጠኛ የሽብር ተግባሩን ግን ሻዕቢያ በአገራችን ላይ ያልቃጣበት ጊዜ አለ ማለት ይቸግራል። የሻዕቢያ መንግሥት በነውጥ፣ በጦርነትና በሽብር አባዜ ተለክፎ በቀውስ ሁኔታ ውስጥ ከመገኘቱ ጋር ተያይዞ የሚመራት ኤርትራም ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፋ ሁኔታ ውስጥ ትገኛለች።

ኤርትራ በሻዕቢያ መንግሥት የቀውስ አመራር ላይ መገኘቷን የሚያረጋግጠው ሌላው አብነት በሻዕቢያ አገዛዝ የተማረሩ ኤርትራውያን በየቀኑ ወደአገራችን የሚያደርጉት ስደት ዋነኛው ማሣያ ነው። ለዚያውም ከሻዕቢያ ጥብቅ የድንበር ጥበቃና ድንበር ሲያቋርጡ ቢገኙ ሊወሰድባቸው የሚችለውን የግድያ እርምጃ ተቋቁመው አምልጠው ማለት ነው።

በዚሁ ወቅት ወደ ሃምሣ ሺህ የሚጠጉ ኤርትራውያን ስደተኞች በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በመጠለያ ካምፕ ውስጥ ብቻ እንደሚገኙ ያመለከተው የድርጅቱ የስደተኞች ጉዳይ ፅህፈት ቤት 49 ሺህ የሚሆኑት ደግሞ ትግራይ ውስጥ ባሉ ሦስት ካምፖችና አፋር አካባቢ ደግሞ ከኅብረተሰቡ ጋር ተቀላቅለው በመኖር ላይ መሆናቸውን አስታውቆ ነበር።

ሻዕቢያ በአገር ውስጥ አመራሩ የፈጠረበትን ቀውስና በሕዝቡ ዘንድ ያስከተለው ምሬት የፈጠረበትን አለመረጋጋት ለመሸሸና አጀንዳ ለማስቀየር አንዴ ኢትዮጵያ ውስጥ፤ ሌላ ጊዜ ሶማሊያ፤ ጥቂት ቆይቶ ደግሞ ኬንያ፤ አልሆን ሲል ደግሞ ጅቡቲ

ውስጥ በመግባት የተጠናወተውን የሽብርና ቀውስ የመፍጠር ሱሱን እየተወጣ ይገኛል።

የሻዕቢያ አመራሮች በዓመቱ መጀመሪያም ሆነ ነግቶ ሲጠባ እቅድ ነድፈው የሚንቀሳቀሱት በዋነኛነት በኢትዮጵያ ቀጥሎ ደግሞ በሌሎች ጎረቤት አገራት ላይ ስለሚከፍቱት የሽብርና የትንኮሳ ስትራቴጂያካዊ እቅድ በማውጣት ነው።

ሁላችንም የምናጭደው የዘራነውን ነውና ኤርትራ ሁሌም ቢሆን በዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃንም ሆነ የተባበሩት መንግሥታትን ጨምሮ በተለያዩ የዓለም አቀፍ ተቋማት በሚወጡ ሪፖርቶች ላይ ስሟ የሚነሳው ጠብ አጫሪ አመራሮቿ አገራቸውን ጨምሮ በጎረቤት አገራትና አልፎም በአፍሪካ በፈጠሩት ብጥብጥ፣ ሁከትና ሽብር ብዛት ነው።

ኢትዮጵያ በፈጣንና በተከታታይ ሁኔታ እያስመዘገበች ባለው ኢኮኖሚያዊ እድገት፣ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ከሚያሳኩ ታዳጊ አገራት በቀዳሚነት በመገኘቷና እንዲሁም በውስጧ ባለው ሠላምና መረጋጋት የዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን ትኩረትን መሳቧ ገሃድ እየሆነ መጥቷል። ይህም ብቻ አይደለም፤ በአፍሪካ ቀንድ ሠላምና መረጋጋት እንዲፈጠር ከምታደርገው ጥረት በተጨማሪም በክፍለ አህጉሩ ተፈጥሯዊም ሆነ ሰው ሰራሽ ችግር በሚፈጠርበት ወቅት የጎረቤት አገራት ሕዝቦች መጠለያ ፍለጋ የሚሰደዱት ወደ ኢትዮጵያ ነው።

በቅርቡ እንኳ በአፍሪካ ቀንድ በ60 ዓመታት ውስጥ ያልተከሰተ የተባለለት የድርቅ አደጋ ባስከተለው ረሃብ በርካቶች ለችግር ሲዳረጉ በዋነኛነት የጎረቤት ሶማሊያ ዜጎች የፈለሱት ወደ ኢትዮጵያ ነው። ኢትዮጵያ እነዚህን ስደተኞች ለመቀበልና ለማስተናገድም በደቡባዊ ኢትዮጵያ ዶሎ አዶ ላይ ብቻ አራት የመጠለያ ጣቢያዎችን አቋቁማ  እስከ 40 ሺህ ስደተኞችን ተቀብላ ነበር ።

በኬንያም እንዲሁ በድርቅ የተጎዱ ዜጎች ወደ ኢትዮጵያ ከመሰደዳቸው በተጨማሪ እጅግ አስገራሚ የሆነው ደግሞ ሰሞኑን የተለያዩ መገናኛ ብዙኃን ይፋ ባደረጉት ዘገባ ላይ እንደተገለፀው በጠረፍ የኬንያ ግዛት የሚኖሩ ኬንያውን በእርስ በእርስ

የሚፈጠሩ የጎሣ ግጭቶችን ሸሽተው ወደ ኢትዮጵያ ከተሞች በስደት የመግባታቸው ጉዳይ ነው።

ቀደም ሲል እንደተገለፀው በአገራቸው ያለውን ነውጠኛና ጦረኛ አመራር ሸሽተው ወደ ኢትዮጵያ በስደት የሚገቡ ኤርትራውያን ስደተኞችን አገራችን በእንክብካቤ ከመያዝ አልፎ ሰርተውና ተምረው የሚኖሩበት ምቹ ሁኔታም ተፈጥሮላቸዋል። የኬንያና ሶማሊያን ጨምሮ በየጊዜው እየፈለሱ ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ስደተኞችም ኢትዮጵያን የሚመርጡት አገራችን ለስደተኞች በምታደርገው እንክብካቤና ለደህንነታቸው የሚያሰጋ ሁኔታ እንደሌለባቸው በመተማመን ነው።

ቀደም ሲል የተጠቀሱት ዋና ዋና ምክንያቶችን ጨምሮ በአሁኑ ወቅት አገራችን በአፍሪካም ሆነ በዓለም መልካም ስምና ዝና ያላት፣ የእድገት፣ የሠላምና የመረጋጋት ምሣሌ ስትሆን ሻዕቢያ ደግሞ በአንፃሩ የሽብርተኝነት፣ የድህነት፣ የብጥብጥና የትርምስ ምሣሌ እየሆነ መምጣቱ በአደባባይ ፀሐይ የሞቀው ጉዳይ ከሆነ ውሎ አድሯል።

ይህ እረፍት የነሳቸው የሻዕቢያ አመራሮችም ኢትዮጵያ ቀደም ሲል በተጠቀሰው መልክ እየገነባች ያለችው ገፅታና እያገኘች የመጣችው ዓለም አቀፍ እውቅናና አድናቆት እረፍት እንደነሳቸው ባለፈው ዓመት ተላላኪዎቻቸውን በመጠቀም በአዲስ አበባ የተካሄደውን የአፍሪካ ሕብረት ጉባኤ ለማጨናገፍ ያደረጉት ሙከራ በግልፅ ያመላክታል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሶማሊያና ኤርትራ ክትትል ቡድን የኤርትራ መንግሥት በአዲስ አበባ የአፍሪካ ሕብረት የመሪዎች ጉባኤ ላይ የቦንብ አደጋ ለመፈፀም ሲንቀሳቀስ እንደነበር በሪፖርቱ አረጋግጧል፡፡

በኤርትራ የሻዕቢያ አመራር በአገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት በማስመዝገብ የዜጎቹን የማህበራዊ አገልግሎት አቅርቦት ማሻሻል ይቅርና ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በአፍሪካ ቀንድ ከ60 ዓመታት ወዲህ ተከስቶ የማያውቀው እጅግ አስከፊ ረሃብና ድርቅ በተከሰተበት ወቅት እንኳን ለጋሾችና ምዕራባውያን መንግሥታት በከፍተኛ

ደረጃ ያስጨንቃቸው የነበረው በድርቅና ረሃብ የተጠቁ ኤርትራውያን ቁጥርና በአገሪቱ የሚያስፈልገውን ያህል እርዳታ በመደበቁ ነበር።

በዓለም ላይ በከፍተኛ ሁኔታ በመቀያየር ላይ ባለው የአየር ንብረት መለዋወጥ ሣቢያ በአፍሪካ ቀንድ የተከሰተው ረሃብና ድርቅ ከከፋ አገዛዙ ጋር ተዳምሮ በርካታ ኤርትራውያን በረሃብ አለንጋ እየረገፉ እንደሆነ መረጃ የነበራቸው ለጋሾችና ምዕራባውያን ይህንን ሁኔታ ይፋ በማውጣት ዜጎቹን ከረሃብ ለመታደግ የሚያስችል እርዳታ ለአገሪቱ እንዲሰጥ የሻዕቢያን አመራሮች ቢጠይቁም እነርሱ ግን ይህን አቃዝ ይደብቃሉ፡፡ ከተለያዩ የጎረቤት እና ከአፍሪካ ቀንድ አገራት ጋር ያለው የውጭ ግንኙነት አሸባሪነትን፣ ጦርነትንና ጠብ አጫሪነት መሠረት ያደረገው የሻዕቢያ አመራር ለዚሁ ፖሊሲው ተግባራዊነት በመንግሥትነት ሥልጣን ላይ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በግዳጅ ብሔራዊ ውትድርና ፕሮግራሙ የኤርትራ ወጣቶችን ለጦርነት እያስገደደ ሲማግድ ቆይቷል፡፡

የሽብር ሙከራና ትንኮሳ በመልካም ሁኔታ እየተለወጠና እየተሻሻለ ባለው የአገራችን ገፅታ ላይና እያደገና እያንሰራራ በመጣው የአገሪቱ የቱሪዝም ዘርፍ ላይ ማነጣጠሩ በእጅጉ ሊያሳስብ የሚገባው ጉዳይ ነው። ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ አገራችን የአፍሪካ መዲና መሆን የቻለችው በተለይም ባላት የማይናወጥ ሠላምና መረጋጋት መሆኑ ከማንም የተሰወረ አይደለም።

ሻዕቢያ ደግሞ ባለፈው ዓመት "አዲስ አበባን እንደ ባግዳድ" በሚል ሊያካሂደው አስቦ በከሸፈበት የሽብር ስትራቴጂ ላይ ተላላኪዎቹ ሲገልፁ እንደነበሩት የሽብር ጥቃቱን የአፍሪካ ሕብረት ጉባኤ በሚካሄድበት ወቅት በመፈፀም የአገራችንን ሠላምና መረጋጋት አደጋ ውስጥ እንዳለ የሚያሳይ መልዕክት ማስተላለፍ ነበር የፈለገው።

ሆኖም በሠላም ወዳድ ሕዝብና የመንግሥት የተቀናጀ ጥረት ስንትና ስንት ጊዜና ሐብት አባክኖ የነደፈው የሽብርና የጦርነት እቅድ ሳይሳካ እንደ ጉም በኖ በደመና ላይ ሊቀር ችሏል።

ባለፈው ሰሞን በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አጣሪ ቡድን ይፋ የሆነው ሪፖርት፤ የኤርትራ መንግሥት ኢትዮጵያን ጨምሮ ክልሉን እያተራመሰና እያሸበረ እንደሚገኝ በማረጋገጡ የኤርትራ ባለሥልጣናት በተለያየ መልኩ እውነታውን ቢያስተባብሉትም  የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በአገሪቱ ላይ ተጨማሪ ማዕቀብ እንዲጥል አስገድዶታል፡፡

የሻዕቢያ መንግሥት ከአልሸባብ ጋር ያለው ቁርኝትና ወዳጅነት ከሽብር እንቅስቃሴው ጋር ተዳምሮም የመንግሥትነት ዕድሜውን በቅርቡ ሊያሳጥረው ይችላል የሚል ትንታኔ የፖለቲካ ተንታኞች ይፋ እያደረጉ ናቸው፡፡

የሻዕቢያው አመራሮች በኤርትራ በመንግሥትነት ሥልጣን ላይ ከወጣበት ጀምሮ እስካሁን ድረስ ባሉት ጊዜያት በአገሪቱ ይህ ነው የሚባል ፋይዳ ያለው የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ባለማከናወናቸውና በአምባገነንና ኢ ዴሞክራሲያዊ በሆነ ጦረኛ አመራራቸው የኤርትራ ዜጎች ለስደት እየተዳረጉ ያሉበት ሁኔታ በከፍተኛ መጠን እየጨመረ መጥቷል።

የሻዕቢያ አመራር በምሥራቅ አፍሪካ ቀንድ የተከተለው የውጪ ግንኙነት ፖሊሲ እንዲጣል ካደረገበት ሁለት ማዕቀብ በተጨማሪ በጎረቤት አገሮችና በዓለም አቀፍ መድረክ ከፍተኛ ተሰሚነት ባላቸው ኃያላን አገሮች ጭምር ተቀባይነት እንዲያጣ አድርጎታል፤ በዚህም የተነሳ የኤርትራ መንግሥት ከመቼውም ጊዜ በላይ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ በሚባል ፖለቲካዊ ውጥረት ውስጥ መግባቱ እየተገለፀ ይገኛል፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞም የኤርትራ መንግሥት ከገባበት የፖለቲካ አጣብቂኝ ውስጥ ለመውጣት ተስፋ የቆረጠ እርምጃ የማይወስድበት የመከራከሪያ ነጥብ ማስቀመጥ የማይቻል በመሆኑ እንቅስቃሴውን የኢትዮጵያ መንግሥት በንቃት ይከታተለዋል፡፡

በአገራችን በሺህዎች መስዋዕትነት እውን የሆነው ሠላምና መረጋጋትና ይህን ተከትሎም በልማታዊ መንግሥት እቅድ ነዳፊነት፣ አስተባባሪነትና በመላው ዜጎች ንቁ ተሳትፎ በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚውና በማህበራዊ አገልግሎት ዘርፎች የተገኙ

እድገቶችና መሻሻሎች መጠበቅ የመከላከያ ኃይላችንን ጨምሮ የመላው ዜጋ ኃላፊነት መሆኑን ሕዝቡ በአግባቡ የተገነዘበበት ወቅት ላይ እንገኛለን፡፡

በኤርትራ መሽገው የሚገኙ ፀረ ሠላም ተላላኪ ኃይሎችን ከምንጫቸው ማድረቅ የሚቻለው ይህንኑ ተመጣጣኝ እርምጃ ኢትዮጵያ በሻዕቢያ ላይ መውሰድ ስትችል ነው።